አዋጅ ቁጥር...../2016

የሀይማኖት ጉዳዮች አዋጅ

የተለያየ የሃይማኖት ተከታዮች ለዘመናት ያዳበሩትን በሰላም አብሮ የመኖር፣ የመከባበር እና የመተማመን መልካም ዕሴቶቻቸውን በማጠናከር ለሀገር ሠላም፣ ልማት እና እድገት የሚኖራቸውን ገንቢ ሚና ማጎልበት አስፈላጊ በመሆኑ፣

የመንግሥትና የሃይማኖት መለያየት መርህ እና የሃይማኖት ነጻነት የሚመራበትን ስርዓት በሕግ መደንገግ በማስፈለጉ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግስት አንቀፅ 55 (1) መሠረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

ክፍል አንድ

ጠቅላላ ድንጋጌዎች

1. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የሃይማኖት ጉዳዮች አዋጅ ቁጥር...../2016" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ ሌላ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ አዋጅ ውስጥ፡-

1) "የሃይማኖት ተቋም" ማለት ሰዎች የመረጡትና የተቀበሉትን ሃይማኖት እና እምነት ይዘው በይፋ ለማምለክ፣ ለመከተል፣ ለመተግበር፣ ለማስተማር፣ ለመማለጽ ወይም ለማስፋፋት እንዲያስችላቸው ያደራጁትና ዓላማው ለትርፍ ያልሆነ በሚኒስቴሩ ተመዝግቦ ወይም በሕግ ተቋቁሞ ሕጋዊ ሰውነት የተሰጠው የሃይማኖት እና የእምነት ተቋም ሆኖ ማኅበር፣ አገልግሎት እና ወይም መሰል አደረጃጀቶችን ያጠቃልላል፡፡
2) "አደባባይ" ማለት ሃይማኖታዊ ስርዓት ሊከናወን የሚችልበት በሚመለከተው አካል የተፈቀደ ቦታ ነው፡፡
3) "በአደባባይ የሚከበር በዓል" ማለት በአደባባይ የሚከበር ሃይማኖታዊ በዓል፣ ሃይማኖታዊ ትምህርት፣ የጋራ ፀሎት፣ ሃይማኖታዊ የገንዘብ መሰብሰቢያ ኩነት፣ ሃይማኖታዊ ጉባኤ፣ የአምልኮ ስርዓት፣ ሃይማኖታዊ ባዛር እና ሌሎች መሰል ኩነቶችን ያካትታል፡፡

Scanned by CamScanner

4) "የትምህርት ተቋም" ማለት ባለቤትነቱ የግል፣ የመንግስት ወይም የህዝብ የሆነ ቅድመ መደበኛ ወይም መደበኛ ትምህርት ቤት ወይም ከፍተኛ የትምህርት ተቋም ነው፡፡

5) "የሃይማኖት ከፍተኛ የትምህርት ተቋም" ማለት ሃይማኖታዊ ትምህርትን በኮሌጅ ወይም በዩኒቨርሲቲ ደረጃ ለመስጠት በሃይማኖት ተቋም የተቋቋም የትምህርት ተቋም ነው።

6) "ሚኒስቴር" ማለት የሰላም ሚኒስቴር ነው፡፡

7) "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግሥት አንቀጽ 47 የተቋቋመ ማንኛውም ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ ከተማ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፡፡

8) ለዚህ አዋጅ ዓላማ ሃይማኖት የሚለው አገላለፅ እንደአግባብነቱ ዕምነትንም ይጨምራል።

9) ማንኛውም በወንድ ጾታ የተገለጸው የሴትምን ጾታ ያካትታል፡፡

3. የተፈጻሚነት ወሰን

ይህ አዋጅ በመላ አገሪቱ ተፈጻሚ ይሆናል።

4. ዓላማ

አዋጁ የሚከተሉት ዓላማዎች አሉት፡-

1) የሃይማኖት እና እምነት ነፃነት ጥበቃ እና አተገባበር የሚመራበት ግልጽ ስርዓት በመዘርጋት የዜጎችን የሃይማኖት እና እምነት ነጻነት ማረጋገጥ፣

2) የሃይማኖት ነጻነት እና እኩልነትን ማረጋገጥ፣

3) የሃይማኖት ተቋማት የሚመዘገቡበትን እና እውቅና የሚያገኙበትን ሥርዓት መፍጠር፣

4) የሃይማኖት ብዝሀነት እንዲከበር ማድረግ እና የመቻቻል ባህልን ማሳደግ፣

5) የመንግስት እና ሃይማኖት ግንኙነት የመንግስት እና ሃይማኖት መለያዬት መርህን ባከበረ መልኩ የሚመራበትን ስርዓት መዘርጋት።

ክፍል ሁለት

ስለሃይማኖት ተቋማት ምዝገባ፣ መብት እና ግዴታ

5. የሃይማኖት ተቋማት ምዝገባ

Scanned by CamScanner

1) በሌላ ሕግ ሀጋዊ ሰውነት ካገኙት በስተቀር ማንኛውም የሀይማኖት ተቋም መተዳደሪያ ደንብን ጨምሮ ይህን አዋጅ ተከትሎ ሚኒስቴሩ በሚያወጣው መመሪያ የተቀመጡ መስፈርቶችን አሟልቶ መመዝገብ አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) መሠረት የተመዘገበ የሃይማኖት ተቋም ሕጋዊ ሰውነት ያገኛል፡፡

6. ምዝገባ የሚከለከልባቸው ምክንያቶች

1) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም በሚከተሉት ሁኔታዎች ምዝገባ ሊከለከል ይችላል፡፡

ሀ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 5 ላይ የተመለከቱ መስፈርቶችን ሳያሟላ ሲቀር፣

ለ) የሃይማኖት ተቋሙ የሚመዘገብበት ስም ወይም አርማ ከሌላ ከተመዘገበ ተቋም ስያሜ ወይም አርማ ጋር የሚመሳሰል ወይም ለህግ ወይም ለሞራል ተቃራኒ ከሆነ፣

ሐ) የሃይማኖት ተቋሙ ዓላማ ከዜጎች መሰረታዊ መብቶች፣ ነፃነት፣ ደህንነት፣ ሰላም፣ ጤና፣ የህዝብ ሞራል እና መንግስትና ሃይማኖት መለያየት መርህ ጋር የሚጋጭ ከሆነ።

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (1) ላይ የተጠቀሰው ቢኖርም ማንኛውም ሰው በጸታ፣ በቋንቋ፣ በዘር ወይም በማኅበራዊ አመጣጡ፣ በፖለቲካ አመለካከቱ ወይም ማንኛውንም ተመሳሳይ ሁኔታ መሠረት በማድረግ ምዝገባ አይከለከልም፡፡

7. በምዝገባ ማመልከቻ ላይ ውሳኔ ስለመስጠት

1) ሚኒስቴሩ በዚህ አዋጅ መሠረት ለምዝገባ ማመልከቻ ከቀረበበት ቀን ጀምሮ በ30 የስራ ቀናት ውስጥ ተገቢውን ውሳኔ ይሰጣል፡፡

2) ሚኒስቴሩ በዚህ ሕግ መሠረት የተቀመጡትን መስፈርቶች አሟልተው የቀረቡ ተቋማትን በመመዝገብ የምስክር ወረቀት ይሰጣል፡፡

3) ሚኒስቴሩ የተመዘገቡ ተቋማትን የመረጃ ቋት ላይ በመመዝገብ በድረ ገጽ ላይ ለሕዝብ ይፋ ያደርጋል።

4) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) መሠረት የሚሰጠው የምዝገባ የምስክር ወረቀት የሀይማኖት ተቋሙን ስም፣ አድራሻ፣ የተመዘገበበት ቀን እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን መያዝ አለበት፡፡

5) ሚኒስቴሩ የምዝገባ ጥያቄውን ውድቅ ካደረገው ምክንያቶቹን በጽሁፍ ለአመልካቹ ማሳወቅ ይኖርበታል፡፡

Scanned by CamScanner

6) በዚህ አንቀፅ መሠረት በተሠጠ ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ወገን የውሳኔው ግልባጭ ከደረሰው ቀን ጀምሮ በ30 ተከታታይ ቀናት ውስጥ ቅሬታውን ሚኒስቴሩ ለሚመድበው ቅሬታ ሰሚ አካል ማቅረብ ይችላል፡፡

7) የተቋሙ የበላይ ኃላፊ ወይም ሰልጣን የተሰጠው የስራ ኃላፊ ወይም ሠራተኛ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (6) መሠረት ቅሬታ የቀረበለት ቅሬታ ሰሚ አካል በሚያቀርበው የውሳኔ ሀሳብ መሰረት ቅሬታው በቀረበ በ30 ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፡፡

8) በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (7) መሠረት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ውሳኔው በደረሰው በ30 ቀናት ውስጥ ለከፍተኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ ይችላል፣ ፍርድ ቤቱ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ይሆናል፡፡

8. <u>ከምዝገባ ስለመሰረዝ</u>

1) የሃይማኖት ተቋም ከሚከተሉት በአንዱ ምክንያት በሚኒስቴሩ ከምዝገባ ሊሰረዝ ይችላል፡-

ሀ) በተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ ላይ ስልጣን በተሰጠው አካል ጥያቄው ሲቀርብ፣

ለ) በፍርድ ቤት ምዝገባው እንዲሰረዝ በህግ አግባብ ሲወሰን፣

ሐ) በዚህ አዋጅ የተቀመጡትን የምዝገባ መስፈርቶች ሳያሟላ ተመዝግቦ ከተገኘ፣

መ) በዚህ አዋጅ አንቀጽ 13 መሰረት የተከለከሉ ተግባራት ላይ ተሳትፎ ሲገኝ፣

ሠ) በዚህ አዋጅ መሰረት በሚፈጠረው ውሀደት፣ መጠቃለል ወይም መለወጥ ምክንያት ህጋዊ ሰውነት ሲያጣ።

2) በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚደረገው የምዝገባ ስረዛ የተቋሙ ህጋዊ ሰውነት ማጣትን ያስከትላል፡፡

3) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሰረት የተሰረዘውን ተቋም ስም እና የስረዛ ምክንያት በድረ ገጹ ለዝዝብ ይፋ ያደርጋል፡፡

9. <u>ስለሃይማኖት ተቋማት ጎብረት፣ውህደት፣ መጠቃለል እና መለወጥ</u>

Scanned by CamScanner

1) ተመዝግበው ሕጋዊ ሰውነት ያገኙ ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የሃይማኖት ተቋማት ጎብረት መመሥረት ከፈለጉ የሚመሰረተው የጎብረት ተቋም ሚኒስቴሩ በመመሪያ የሚወስናቸውን መስፈርቶች በማሟላት መመዝገብ አለበት፡፡

2) ተመዝግበው ህጋዊ ሰውነት ያገኙ ሁለት ወይም ከዛ በላይ የሆኑ የሃይማኖት ተቋማት የቀድሞ ህልውናቸውን በመተው ውህደት በመፍጠር እንደ አዲስ መመዝገብ ይችላሉ፡፡

3) አንድ የሃይማኖት ተቋም የነበረውን ህልውና በመተው በሌላ ሃይማኖት ወይም እምነት ተቋም ስር ለመጠቃለል ሲፈልግ የወሰደውን የሕጋዊ ሰውነት ማረጋገጫ የምስክር ወረቀቱን በመመለስና የነበረውን ህልውና በመተው መጠቃለል ይችላል፡፡

4) የንብረት አስተዳደርን በተመለከት በጎብረቱ፣ በተዋሀዱት ወይም በተጠቃለሉ ተቋማት መተዳደሪያ ደንብ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

10. <u>የሃይማኖት ተቋም ስያሜ እና ዓርማ</u>

1) ማንኛውም የሀይማኖት ተቋም የሚፈልገውን ሥያሜ ወይም ዓርማ ለተቋሙ መጠሪያ እንዲሆን መምረጥ ይችላል፡፡

2) የሀይማኖት ተቋም የሚይዘው ስያሜ ቀድሞ በሌላ ተቋም የተመዘገበ ወይም ከሌላ ሰው ስም ጋር ተመሳሳይ መሆን የለበትም፡፡

3) ተቋሙ ዓርማ (ምልክት) መጠቀም ከፈለገ ከሚያስመዘግበው ስም ጋር አያይዞ ማቅረብ አለበት፡፡

4) የሚመዘገበው ስም እና ዓርማ/ምልክት በተመዝጋቢው ወጪ ሀገር አቀፍ ስርጭት ባለው ጋዜጣ በማስታወቂያ ታትሞ እንዲወጣ ይደረጋል፡፡

5) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም ስያሜና ዓርማ/ምልክት መጠቀም የሚችለው በጋዜጣ ታትሞ እንዲወጣ ከተደረገና በሚኒስቴሩ ከተመዘገበ በኋላ ነው፡፡

6) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (5) መሠረት ማስታወቂያው በጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ በሃያ ተከታታይ የስራ ቀናት ውስጥ የተቋሙን ስም እና ዓርማ/ምልክት ምዝገባ የሚቃወም ሰው ካልቀረበና ስም እና ዓርማውን/ምልክቱ እንዳይመዘገብ የሚያደርግ ሕጋዊ ምክንያት ከሌለ ሃያ ተከታታይ የስራ ቀናት ጊዜው እንዳለቀ ተመዝጋቢ ተቋሙ ያቀረበውን ስም እና ዓርማው ይመዘግባል፡፡

7) ሚኒስቴሩ የተቋሙን ስም እና ዓርማ እንዲመዘግብ የቀረበለትን ጥያቄ ያልተቀበለው እንደሆነ ያልተቀበለበትን ምክንያት በመግለጽ ለተመዝጋቢው በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡

Scanned by CamScanner

8) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም ቀደም ሲል አስመዝግቦት የነበረውን ስም፣ ዓርማ/ምልክት መለወጥ ወይም ማሻሻል ከፈለገ ሊለውጠው ወይም ሊያሻሽለው የፈለገውን አዲስ ስም፣ ዓርማ ወይም ምልክት በሥራ ላይ ከማዋሉ በፊት ለሚኒስቴሩ ቀርቦ በዚህ አንቀጽ መሰረት የሚፈጸም ይሆናል፡፡

9) የተቋም ስያሜ ወይም ዓርማ/ምልክት ከሕግ እና ከሀገሪቱ ሞራል ጋር ተቃራኒ መሆን የለበትም፡፡

11. <u>የሃይማኖት ተቋም መብቶች</u>

ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም የሚከተሉት መብቶች አሉት፡-

1) ሃይማኖቱና ዕምነቱን ያለማንም ጣልቃ ገብነት በነጻነት እና በእኩልነት የመተግበር፣ የማስተማር እና የመግለጽ ወይም የማሳወቅ፣

2) ሃይማኖቱንና ዕምነቱን ለማስፋፋትና ለማደራጀት የሚያስችለውን የሃይማኖትና ዕምነት ትምህርትና የአስተዳደር ተቋማት የማቋቋም፣

3) በሀገር ሰላም፣ ልማት እና እድገት ግንባታ ላይ የመሳተፍ፣

4) መልካም ዕሴቶቹን በተናጠልና በጋራ የማጎልበት፣

5) የተቋቋመበትን ሃይማኖታዊ ዓላማ ለማሳካት እንዲያስችሉት በሃገሪቱ ሕጎች መሠረት ተገቢውን አገልግሎት ከመንግስት ተቋማት የማግኘት።

12. <u>የሃይማኖት ተቋም ግዴታዎች</u>

1) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም የሚከተሉት ግዴታዎች አሉበት፡-

ሀ) ሕገ-መንግሥቱን እና ሌሎች የሀገሪቱን ሕጎች የማክበር፣

ለ) በተከታዮቹ እና በሌሎች ሃይማኖት ተከታዮች መካከል ሰላምና መከባበር እንዲሰፍን የመስራት፣

ሐ) በሥሩ የሚገኙ አደረጃጀቶች ሕግን ተከትለው እየሰሩ መሆናቸውን የመከታተልና የማረጋገጥ፣ ችግሮች ሲያጋጥሙ በሰላማዊ መንገድ እንዲፈቱ ማድረግ፣

መ) የተቋሙን የገቢ አሰባሰብና የወጪ አስተዳደር በሕጋዊ መንገድ እንዲከናወን ማድረግ፣

Scanned by CamScanner

ሠ) በሃይማኖት ሽፋን የሚፈፀሙ ወንጀሎችን የመከላከል፣ ወንጀሉ የተፈፀመ፣ እየተፈፀመ ወይም ሊፈፀም የሚችል ስለመሆኑ ባወቀ ጊዜ ለሚመለከተው የፀጥታ ወይም የፍትህ ተቋም መረጃ የመስጠት፣

ረ) የምዝገባ የምስክር ወረቀቱን በዋናው ጽ/ቤትና በየአደረጃጀቶቹ በማሰረጃነት እንዲገኝ የማድረግ፣

ሰ) የአመራር ውሳኔ ለሚጠይቁ ተዛማጅ አገልግሎቶች ውሳኔ የሚሰጠውን አካል በተቋሙ መተዳደሪያ ደንብ በግልፅ ማስቀመጥ፣

ሸ) ተቀባይነት ያለው የሂሳብ አያያዝ እና አዲት ሥርዓት የመዘርጋት እና የአዲት ሪፖርት ለሚኒስቴሩ የማቅረብ።

2) ለዚህ አንቀፅ ዓላማ "አደረጃጀት" ማለት በአንድ ሃይማኖት ተቋም ስር የሚተዳደር ወይም የሚመራ በየተዋረዱ ያለ እርከን ወይም መዋቅር ነው።

13. <u>የተከለከሉ ተግባራት</u>

ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም የሚከተሉትን ተግባራት ከማድረግ መቆጠብ አለበት: -

1) ከተቋቋመበትና ከተመዘገበበት ሃይማኖታዊ ዓላማ ውጭ መንቀሳቀስ፣
2) የራሱን ሃይማኖት ሌላ ሰው በግድ እንዲያምን ወይም እንዲከተል የማድረግ፣
3) በመንግስት ተቋማት፣ መንግሥታዊም ሆነ በግል መደበኛ የትምህርት ተቋማት ሃይማኖታዊ ሰበካ ወይም ቅስቀሳ ማድረግ፣
4) ከህዝብ ደኅንነት፣ ሰላም፣ ጤና፣ ትምህርትና ሞራል እንዲሁም የዜጎችን መሠረታዊ መብትና ነፃነቶች ተጻራሪ የሆኑ ተግባራትን መፈጸም፣
5) ሃይማኖትን ሽፋን አድርጎ በሚፈፀም ወንጀል ወይም ለማህበረሰቡ ሰላምና ፀጥታ ስጋት በሆነ እንቅስቃሴ እና ተግባር መሳተፍ ወይም መደገፍ፣
6) በሕገ-ወጥ የገንዘብ ዝውውር መሳተፍና መተላለፊያ መሆን፣
7) የሌላውን ሐይማኖት ማናናቅ፣ መስደብ፣ ማዋረድ፣ በአማኞች መካከል ግጭትን ሊያስነሱ የሚችሉ መልዕክቶችን በማናቸውም መንገድ ማስተላለፍ፣
8) በሕግ በተከለከሉ ቦታዎች ሃይማኖታዊ ቅስቀሳዎችን ማካሄድ፣

Scanned by CamScanner

9) ሌሎች በህግ በተከለከሉ ተግባራት መሳተፍ።

ክፍል ሶስት

የሃይማኖት በዓላት አከባበር፣ ሕዝባዊ ሀብቶች አጠቃቀም እና የመንግስትና ህዝባዊ ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ

14. ሃይማኖታዊ በዓላት በአደባባይ ስለሚከበሩበት ሁኔታ

1) በአደባባይ የሚከበር ሃይማኖታዊ በዓል በሃይማኖት ተቋሙ ስነ ስርዓት መሰረት መከበር አለበት፡፡
2) በአደባባይ የሚከበር ሃይማኖታዊ በዓል ለሰላም ወይም ለሕዝብ ደህንነት ስጋት በማይፈጥር፣ የሕዝብና የመንግስት ንብረት ደህንነት እና የሌሎችን ሰዎች መብት በማይጥስ መልኩ መከበር አለበት፡፡
3) የአደባባይ በዓል በተፈቀደው ቦታ ብቻ መደረግ አለበት፡፡
4) የአደባባይ በዓል ለማክበር የሚቀርበው ጥያቄ የሀይማኖቶችን እኩልነት እና ነፃነት ባከበረ መልኩ ያለአድልዎ መስተናገድ አለበት፡፡
5) በመንግስት ኃላፊዎች በሃይማኖታዊ በዓል ሊተላለፍ የሚችል የእንኳን አደረሳችሁ መልዕክት የሃይማኖት እኩልነትን እና የመንግስትና ሃይማኖት መለያየት መርህን ያከበረ መሆን አለበት፡፡
6) የመንግስት ኃላፊዎች መንግስትን ወክለው በሃይማኖታዊ በአላት አከባበር ላይ መገኘት አይችሉም፡፡

15. የአምልኮ እና አስተምህሮ አተገባበር

1) ሀይማኖታዊ አምልኮ ወይም አስተምህሮ በአደባባይ የሚደረግ በሆነ ጊዜ ሃይማኖታዊ ሥርዓቱ እንዲከናወን በተፈቀደበት ቦታ ብቻ የተወሰነ መሆን አለበት፡፡
2) በመኖሪያ ቤቶች፣ በትምህርት ትቤቶች እና በህክምና ማዕከላት አካባቢ የሚደረግ አምልኮ በአካባቢ ጥበቃ ህግ የተቀመጠውን የድምጽ መጠን ያከበረ መሆን አለበት፣
3) በየትኛውም መንገድ የሚሰጡ ወይም የሚተላለፉ ሃይማኖታዊ ትምህርቶች የሌሎችን ሃይማኖት ወይም እምነት የማያንቋሽሹ፣ በህዝቦች መካከል ፀብና መቃቃር የማይፈጥሩ፣

Scanned by CamScanner

ጥላቻ የማያሳድሩ፣ የሌሎችን ሃይማኖት የማያንቋሽሹ ወይም የሌላን ሰው መብት የማይነኩ መሆን አለባቸው ።፡

4) ሃይማኖታዊ ስነ ስርዓት ለማከናወን ካልተፈቀደ በስተቀር ማስተማርን ጨምሮ ሃይማኖታዊ ተግባራትን በህዝብ መሰብሰቢያ ቦታዎች፣ በሌላ ሃይማኖት ተቋም አካባቢ፣ መኖሪያ አካባቢዎች፣ ማንጎዳዎች፣ ትምህርት ቤቶች፣ የአየር መንገድ ተርሚናሎች፣ ወታደራዊ ካምፕ፣ ህክምና ቦታዎች ወይም በሌሎች የህዝብ አገልግሎት መስጫ ቦታዎች መፈጸም የተከለከለ ነው።

16. የአምልኮ ወይም የመቃብር ቦታ አሰጣጥ

1) የሃይማኖት ተቋማት መሬት አቅርቦት በመሬት አጠቃቀም እና የሊዝ ህጎች መሰረት የሚወሰን ይሆናል።፡
2) በተለያዩ ቤተ እምነቶች መካከል የሚኖረው ርቀት ቢያንስ 500 ሜትር መሆን አለበት።፡
3) የአምልኮ ወይም መቃብር ቦታ በተጠየቀበት አካባቢ ለሃይማኖት ተቋሙ ለተመሳሳይ ዓላማ የተሰጠ ቦታ አለመኖሩ ወይም ተጨማሪ ቦታ መስጠት አስፈላጊ መሆኑ መረጋገጥ አለበት።፡
4) በከተሞች ለአምልኮና መቃብር የሚሰጥ ቦታ የከተማውን የእድገትና የልማት እቅድ ወይም ማስተር ፕላን የማይቃረን መሆን አለበት።፡
5) ለአምልኮ ሆነ ለመቃብር የተሰጠ ቦታ ለተፈቀደለት ዓላማ ብቻ መዋል አለበት።፡
6) ለአምልኮ ወይም ለመቃብር የሚሆን ቦታ አሰጣጥ እና ቦታው መልሶ ሊነጠቅ ስለሚችልበት ሁኔታ ስልጣን በተሰጠው አካል ዝርዝር መመሪያ ሊወጣ ይችላል።፡

17. የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ

1) የመንግስት ተቋማት ከሀይማኖት ወገኝተኝነት ነፃ ሆነው እና የመንግስትና ሀይማኖት መለያየት መርህን ተከትለው አገልግሎት መስጠት አለባቸው።፡
2) ማንኛውም የመንግስት አመራር ወይም ባለሙያ ኃላፊነቱን ከሃይማኖት እና እምነት ተጽዕኖ ነጻ ሆኖ መወጣት አለበት።፡
3) የመንግስት ተቋማት አገልግሎት አሰጣጥ የትኛውንም ሃይማኖት ወይም እምነት የማይወክል ወይም የሃይማኖት ወይም እምነት መገለጫን የማያንጸባርቅ መሆን አለበት።፡
4) በመንግስት ተቋም ቅጥር ግቢ ወይም ቢሮ ውስጥ በመሆን ሃይማኖታዊ ትምህርትን ማስተማር ወይም በቡድን የአምልኮ ተግባር ማከናወን ክልክል ነው።

Scanned by CamScanner

5) በመንግስት ተቋማት ሀይማኖትን የሚያንፀባርቁ ምልክቶች፣ ዓርማዎችን እና ጽሑፎችን መስቀል ወይም መለጠፍ ክልክል ነው።

6) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) ድንጋጌ የተቋሙን ተግባር ወይም ሊላውን የእምነት ተከታይ ሊያውክ በማይችል መልኩ በግል የሚደረግ አምልኮን ወይም ፀሎትን ወይም በጋራ የሚደረግ የማዕድ ፀሎትን የሚከለክል አይሆንም።

7) ለዚህ አንቀጽ ድንጋጌዎች ጥሰት የሚወሰዱ አስተዳደራዊ እርምጃዎች የመንግስት ተቋማት በሚያወጡት መመሪያ ይወሰናል።

18. መንግስታዊ ባልሆነ ተቋም ወይም ህዝባዊ ድርጅት ስለሚሰጥ አገልግሎት

1) ማንኛውም መንግስታዊ ያልሆነ ተቋም ወይም ሕዝባዊ ድርጅት አገልግሎት ጠያቂው የሚከተለውን ሃይማኖት ወይም እምነት ግምት ውስጥ ሳያስገባ አገልግሎቱን ለሁሉም እኩል መስጠት አለበት።

2) ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ወይም ህዝባዊ ድርጅት ከየትኛውም ሃይማኖት ወይም እምነት ዓላማና ግብ ነፃ ሆኖ መቋቋም እና መስራት አለበት።

3) ለዚህ አንቀፅ ዓላማ "ህዝባዊ ድርጅት" ማለት ከመንግስት ፈቃድ አግኝቶ ለህዝብ አገልግሎት የሚሰጥ ተቋም ነው።

19. ትምህርት እና ሃይማኖታዊ ተግባራት

1) ትምህርት በየትኛውም ሁኔታ ከሃይማኖት ወይም እምነት ተፅእኖ ነጻ በሆነ መንገድ መሰጠት አለበት።

2) መደበኛ ትምህርት በሚሰጡ የመንግስት ወይም የግል ተቋማት የሚሰጠው ትምህርት ሃይማኖታዊ ይዘት የሌለው መሆን አለበት።

3) የትምህርት መሳሪያዎች ወይም መጻህፍት የትኛውንም ሃይማኖት ወይም እምነት የማያንፀባርቁ መሆን አለባቸው።

4) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (2) ድንጋጌ ስለሀይማኖታዊ የጋራ እሴቶች ማስተማርን አይከለክልም።

5) በማንኛውም የትምህርት ተቋም ቅጥር ግቢ ውስጥ ሃይማኖታዊ ትምህርትን ማስተማር ወይም በቡድን ማምለክ የተከለከለ ነው።

6) ሀይማኖታዊ አለባበሶች ማንነትን ለመለየት በሚያስችል መልኩ ጥቅም ላይ ሊውሉ ይገባል።

Scanned by CamScanner

7) የዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ (5) ድንጋጌ የትምህርት አሰጣጡን ወይም ሌላውን የእምነት ተከታይ ሊያውክ በማይችል መልኩ የሚደረግ አምልኮን ወይም ፀሎትን የሚከለክል አይሆንም።

8) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀፅ (7) ዝርዝር አፈጻፀም እንደ አግባብነቱ የትምህርት ሚኒስቴር ወይም የትምህርት ቢሮ በሚያወጣው መመሪያ ይወሰናል።

20. የሃይማኖት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ትምህርት እውቅና እና እቻ ግምት አሰጣጥ

1) መንግስት በሀይማኖት ከፍተኛ ትምህርት ተቋማት ለሚሰጥ ትምህርት እውቅና እና የትምህርት ማስረጃ እቻ ግመታ ይሰጣል፡፡

2) መንግስት በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ (1) መሰረት እቻ ግመታ የሚሰጠው የሚያወጣው ዝቅተኛ መመዘኛ ተሟልቶ ሲገኝ እና ለእውቅናው በተቋማቱ ጥያቄ ሲቀርብ ነው፡፡

3) የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) እና (2) ድንጋጌዎች አፈጻጸም የሚኒስትሮች ምክር ቤት በሚያወጣው ደንብ ይወሰናል፡፡

21. የሠራተኞች ቅጥርና አስተዳደር

1) የህዝብ አገልግሎት በሚሰጥ የመንግስት ተቋም፣ የግል ወይም ህዝባዊ ድርጅት የሚደረግ የሠራተኛ ቅጥር፣ ምደባ፣ ዝውውር፣ እድገት ወይም አስተዳደር የሀይማኖት ልዩነትን መሰረት ያደረገ መሆን የለበትም፡፡

2) በሃይማኖት ተቋማት የሚደረገው የሠራተኛ ቅጥር እና አስተዳደር የሠራተኛውን ሰብዓዊ መብት እና የሠራተኛ ጥበቃ ዝቅተኛ መመዘኛ ያከበረ መሆን አለበት፡፡

ክፍል አራት

በሃይማኖት ተቋም ውስጥ ስለሚከሰቱ አለመግባባቶች አፈታት፣ የገቢ ምንጭ እና የፋይናንስ አስተዳደር

22. በሃይማኖት ተቋም ውስጥ ስለሚከሰቱ አለመግባባቶች አፈታት

1) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም በውስጡ የሚፈጠሩ አለመግባባቶችና ቅሬታዎች የሚፈቱበት ስርዓት መዘርጋት አለበት፡፡

2) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) ድንጋጌ መሰረት የመጨረሻ ውሳኔ ባገኘ ጉዳይ ላይ ቅሬታ ያለው አካል ስልጣን ላለው ፍርድ ቤት ይግባኝ የማለት መብት አለው።

Scanned by CamScanner

3) የሃይማኖት ተቋሙ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (1) በተመለከተው አግባብ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል አደረጃጀት ወይም አሰራር አለመዘርጉ ሃይማኖት ተቋሙ በሰጠው ውሳኔ ላይ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብን የሚከለክል አይሆንም።

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (2) መሰረት ለመደበኛ ፍርድ ቤት ይግባኝ ማቅረብ የሚቻለው ጉዳዩ በፍርድ ቤት ቀርቦ ሊታይ የሚችል እና ከመሰረታዊ የሃይማኖቱ አምልኮ ወይም አስተምህሮና መንፈሳዊ ጉዳይ ጋር የተያያዘ ባልሆነ ጉዳይ ላይ ነው።

23. <u>የሃይማኖት ተቋማት የገቢ ምንጭ እና ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት</u>

1) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም አግባብነት ያላቸው ህጎች በሚፈቅዱት መሰረት በበጎ አድራጎት ወይም ገቢ ማስገኛ ስራዎች ላይ መሰማራት ይችላል።

2) የኃይማኖት ተቋሙ በራሱ የገቢ ማስገኛ ሥራዎችን በሚያከናወንበት ጊዜ ለዚሁ ሥራ የተለየ የባንክ ሒሳብ መክፈት እና የተለየ የሂሳብ መዝገብ መያዝ ይኖርበታል።

3) ማንኛውም የኃይማኖት ተቋም ግልፅ የሆነ የሒሳብ አያያዝ ሥርዓት መከተልና የሒሳብ መዝገብ መያዝ አለበት።

4) የሒሳብ አያያዝ ሥርዓቱ የገቢ፣ ወጭና አጠቃላይ ንብረት ዝርዝርን የያዘ መሆን አለበት።

24. <u>ከውጭ አገር ስለሚሰጥ ድጋፍ</u>

1) ማንኛውም የኃይማኖት ተቋም ከውጭ አገር የሚመጣ የገንዘብ እርዳታ፣ ስጦታ ወይም ሌሎች የገንዘብ ድጋፎችን በህግ ስልጣን ለተሰጠው አካል ማሳወቅ አለበት።

2) ይህ ማሳወቂያ የሚከተሉትን ጉዳዮች መያዝ አለበት፣

ሀ) የለጋሹ ድርጅት ወይም ግለሰብ ስምና አድራሻ፣

ለ) የተለገሰው የገንዘብ፣ ስጦታ ወይም ድጋፍ ዓይነትና መጠን፣

ሐ) ስጦታው ወይም ድጋፉ የተሰጠበት ልዩ ዓላማ፣

መ) ሌሎች ከስጦታው ወይም ድጋፉ ጋር የተቀመጡ ሁኔታዎች፣፣

Scanned by CamScanner

25. የኃይማኖት ተቋማት የአዲት ሥርዓት

1) ማንኛውም የኃይማኖት ተቋም የሃይማኖት ተቋሙ የበጀት ዓመት በተጠናቀቀ በሶስት ወራት ውስጥ የፋይናንስ እንቅስቃሴውን በገለልተኛ አዲተር ማስመርመር አለበት።
2) የአዲት ሪፖርቱ ትክክለኛ የፋይናንስ አሰራርና የገንዘብ አጠቃቀሙንና ግልፀኝነቱን በተመለከተ የአዲተሩን አቋምና የጪሳኔ ሃሳብ መያዝ አለበት።
3) ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም በዚህ አንቀጽ መሰረት የተዘጋጀውን የአዲት ሪፖርት ለሚኒስቴሩ መላክ አለበት።
4) ሚኒስቴሩ በዚህ አንቀጽ መሰረት ከሃይማኖት ተቋማት የደረሰውን የአዲት ሪፖርት አመች በሆነ መንገድ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ አለበት።

ክፍል አምስት

የመንግስት ተቋማት እና ባለድርሻ አካላት ተግባርና ኃላፊነት

26. የትምህርት ተቋማት ኃላፊነት

በየደረጃው የሚገኙ የትምህርት ተቋማት የትምህርት ሥርዓቱ ከሃይማኖት ተጽዕኖ የተላቀቀ መሆኑን የማረጋገጥ ኃላፊነት አለባቸው፡፡

27. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነት

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት አሉበት፡-

1) የሀይማኖት ተቋማት የምዝገባ ስርዓት ይዘረጋል፣

Scanned by CamScanner

2) መስፈርቱን እሚልተው ጥያቄ ለሚያቀርቡ የሃይማኖት ተቋማት ምዝገባ ያከናውናል፣ ይሰርዛል፣ በዚህ አዋጅና አዋጁን ተከትሎ በሚወጣ መመሪያ መሰረት አስተዳደራዊ እርምጃዎችን ይወስዳል፣

3) የሃይማኖት ተቋማት ምዝገባ አግባብ እና ተደራሽ በሆነ ዘዴ ይፋ የሚደረግበት ሁኔታ ያመቻቻል፣ ለሕዝብ ክፍት እንዲሆን ያደርጋል፣

4) በሃይማኖቶች መካከል መልካም ግንኙነትና መስተጋብር እንዲኖር የሚያስችሉ ሥራዎችን ይሰራል፣

5) በተለያዩ ሀይማኖቶችና እምነቶች መካከል ሰላምና መተባበር እንዲሰፍን ለማድረግ አግባብነት ካላቸው አካላት ጋር በመተባበር ይሰራል፣

6) የሃይማኖት ተቋማት በሰላም ግንባታ፣ በልማት፣ ግብረገብነትን ከማጎልበት አንጻር ሚናቸውን እንዲወጡ ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል።፣

28. የሚዲያ ኃላፊነት

1) ማንኛውም የሚዲያ ተቋም የሚከተሉት ኃላፊነቶች አሉበት፡-

ሀ) ሃይማኖታዊ ጉዳዮችን በሚመለከት የሚዘጋጅ ጽሁፍ፣ መረጃ፣ ዘገባና ሌሎች ተያያዥ ተግባራት በገለልተኝነትና የሙያው ሥነ ምግባር በሚጠይቀው አግባብ የማቅረብ፣

ለ) በሀይማኖቶች መካከል ሊኖር የሚገባውን መልካም ግንኙነትና መስተጋብር የሚያውኩ ዘገባዎችን ከማቅረብ የመቆጠብ።፣

2) በሃይማኖት ተቋም የተቋቋመ ሚዲያ በሌሎች ሃይማኖቶች ላይ ወይም በተከታዮች መካከል ጥላቻን፣ ግጭትን፣ አለመተማመንን ሊፈጥር ከሚችል ድርጊት መቆጠብ አለበት።

3) የሚዲያ ተቋማትን ለመቆጣጠር ስልጣን ያለው አካል በሃይማኖት ተቋማት የሚቋቋም ሚዲያ ሊከተለው ስለሚገባ ሥርዓት እና አስተዳደራዊ እርምጃን በተመለከተ መመሪያ ያወጣል።

ክፍል ስድስት

ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

Scanned by CamScanner

29. የውጭ ሀገር ዜጋን ቀጥሮ ስለማሰራት

ማንኛውም የሃይማኖት ተቋም፡-

1) አግባብ ባለው ሕግ መሰረት የመኖሪያና የሥራ ፈቃድ ያልተሰጠውን የውጭ ዜጋ ማሰራት አይችልም ፡፡
2) የውጭ ሀገር ዜጋን ተቀብሎ ለማሰራት የሥራ ፈቃድ ከሚመለከተው አካል ለማግኘት የሚያስችለውን የድጋፍ ደብዳቤ ከሚኒስቴሩ ማግኘት አለበት፡፡

30. ደንብ እና መመሪያ የማውጣት ስልጣን

1) የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ ለማስፈፀም የሚያስፈልግ ደንብ ሊያወጣ ይችላል፡፡
2) ሚኒስቴሩ ይህን አዋጅ እና በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ 1 መሰረት የሚጣውን ደንብ ለማስፈጸም መመሪያ ሊያወጣ ይችላል፡፡

31. ተፈፃሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር የሚቃረን ማንኛውም ሕግ በዚህ አዋጅ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም፡፡

32. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

------ቀን/2016 ዓ.ም አዲስ አበባ

ሳህለወርቅ ዘውዴ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዴሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ፕሬዝዳንት

Scanned by CamScanner